ፓኖራማ ቁጥር 63

የትዝብት አድማስ

መጋቢት 8 ቀን 2001 ዓም

## ጎርፉ እያመለጠ አለቱ ይቀራል
## ሀገርም ታሪክም ሁሉን ይታዘባል

በአርባ ዓመታት ውስጥ ሦስት ሥርዓቶች ተለዋውጠዋል፡፡ "ይሻል" እየሄደ ይባስ ሲመጣ አይተናል፡፡ የተሻለ ሥርዓት ለማምጣት ሲባል የተከፈለውን መሥዋዕት መጠኑንና ጥልቀቱን ማንም በትክክል ሊገምተው አይችልም ፡፡ አሁንም የሀገሪቱ የመከራ ገመድ መቆረጡ ቀርቶ÷እንዲያውም እየተተበተበና እየረዘመ በመሄድ ላይ ነው፡፡ በርከት ያለው ክፍልም÷የገመድ ጉተታውን ጨዋታ ሥራየ- ጉዳይ ብሎ ተያይዞታል፡፡ የሚበጣጠሰውም ቁርጥራጭ ገመድ የሀገሪቱ መከራ ማክተሚያ ምልክት መሆኑ ቀርቶ÷እንዲያውም ጎታቾቹ ለዕርስ በዕርስ መተናነቂያና መሰቃቀያ እያደረጉት ይታያሉ ፡፡ የሀገሪቱ ጠላቶችም ይኸንን እያዩ ዜጎቿ በይበልጥ እንዲጠፋፉና እንዲተናነቁ አዳዲስ የመሰቃቀያ ገመድ እያቀበሏቸው ናቸው ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህ የገመድ ጉተታ በጠላቶቹ መካከል ቢሆን ኖሮ ምንኛ በተደሰተ ነበር? ግን በጠላቶቹ አማካኝነት ወገኖቹ ጉሮሮ-ለጉሮሮ እየተናነቁ የጠላቶቹን ዕድሜ ሲቀጥሉ እያየ የሀዘኑና የትካዜው መጠን እጥፍ ድርብ እየሆነበት በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የውስጥ ጠላቶቹም ÷ከባዕዳን ደመኞቹ ጋር እጅና ጓንት ሆነው በመስራት ሀገሪቱን አጥፍቶ ለመጥፋት የጥድፊያቸውን ፍጥነት እየጨመሩ በመሄድ ላይ ናቸው፡፡መቸም ሀገሪቱን አጥፍቶ በመጥፋት ደረጃ የኞቹን የሚወዳደራቸው እንደሌለ በተግባር አስመስክረዋል፡፡ የዕለቱ አሳሳቢና አጣዳፊ ጉዳይ ሆኖ የተገኘው ግን÷ የእነርሱ አጥፍቶ መጥፋት ሳይሆን ÷ አጥፍተው ሊያጠፏት የተዘጋጁላትን ሀገር ጨርሳ ጠፍታ እንዳትጠፋ ምን መከላከያ መደረግ አለበት

የሚለው ጥያቄ ሆኗል፡፡የእኛ የዕለቱ ጭንቀትና ጥበትም÷አጥፊዎቿ አጥፍተው ሲጠፉ ÷ የቀበሯትን ሀገር እንዴት አድርገን ከከርሰ መቃብሯ ማውጣት እንችላልን ? የሚለው ሆኗል፡፡ ዛሬ ÷ የነገዋን ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ለማጻንና ለማቆየት የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ ÷ ከአድማስ ባሻገር ማየት መቻል ÷ ብቸኛ አማራጩ ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ጭምር መሆኑን መረዳት ይጠበቅበታል፡፡

ለአለፉት18 ዓመቶች በዘረኛ ሥርዓት ውስጥ ስትማቅቅ የቆየችው ሀገር ወዴት አቅጣጫ እንደምታመራ የማይገነዘብ ዜጋ አለ ተብሎ አይታሰብም ፡፡ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ችግሮች ከደቂቅ እስከ ሊህቅ ሁሉም ያውቀዋል፡፡ ችግሩ÷ችግሩን አለማወቁ ሳይሆን አውቆም መፍትሄውን ለመፈለግ እንዳይችል እንደተደገመበት ኃኔል ሰማይ ምድሩ የተደፋበት መሆኑ ነው ፡፡ በአመዛኙ ትኩረት የሚሰጠው ስለአለፈው መከራና አሁን ስላለው ሰቆቃ እንጅ ካለበት ሰቆቃ ተላቅቆ ÷ የነገውን መፍተሄ ለመፈለግ አይደለም ፡፡ ከዛሬው ስቆቃ ሊያላቅቀው ከሚችለው የመፍትሄ ፍለጋ እንዳያተኩር ያላስቻለውን ምክንያት ጠይቆ መልስ ለማግኘት ይጣጣራል ለማለትም አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱ ግለፅ ነው ፡፡ የተተኮሰበት ድኩላ ከአዳኞቹ ሸሽቶ ለማምለጥ ግራ እንደሚጋባና ለመሸሸ የሚያስችለውን አቅጣጫ ለማየት እንደሚጨልምበት ሁሉ÷ አብዛኛው የተቃዋሚ ክፍልም ÷አቅጣጫውን አውቆ ዕርምጃ ለመውሰድ የሚያስችለውን ውሳኔ ለመውሰድ ÷ ዕውቀቱ ብቻ ሳይሆን ቁርጠኝነቱም እንደሌለው አስመስክሯል ፡፡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ÷ በምኞት ፈረስ እየጋለቡ ÷ የተስፋ ዳቦ እየገመጡ ÷በከንቱ ውዳሴ እየተኮፈሱ ÷እርስ በእርስ እየተናኮሩ÷ በተልካሻ ጭራሮ እየተጨፋጨፉና በልተው በጣሉት የሙዝ ልጣጭ ላይ እየተራመዱ አዳልጧቸው በመውደቅ ውጤት ሊመጣ አይችልም ፡፡ እዚህ ላይ ሁለት የማይታበሉ ሀቆች እንዳሉ በዕርግጠኝነት መናገር ይቻላል ፡፡ ይኸውም ኢትዮጵያ የአናብስት ሀገር እንደነበረችና ÷ አሁንም እንደሆነች ሲሆን ÷ ሁለተኛው ሀቅ ደግሞ ÷ኢትዮጵያ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ስትወዳደር÷ በብዛትም÷ በዓይነትም ይሁን በጥራት ÷ በምሁራን ደረጃ የመጀመሪያውን ረድፍ የያዘች መሆኗ ነው ፡፡ እነኝህ ሁለት ብሔራዊ ሀብቶቿ ከጭቆና ቀንበርና

ከድኅነት አረንቋ ሊያወጧት አለመቻለቸው እንቆጭልሽ ሆኖ ቆይቷል። ታዲያ አናብስቷ፥ጠላቶቿን ሰባብረው ከጭቆና ቀንበር ነፃ ካላወጧትና በችሎታቸውና በሙያ ብቃታቸው  በዓለም ደረጃ የሚወዳደሩት ምሁሮቿ ደግሞ ፥ ከድህነት ከድንቁርናም ይሁን ከበሽታ ቁራኛ ካላላቀቋት፥ እነኝህን ተግባራት ማን እውን ሊያደርጋቸው  ይችላል ? መልሱን በብቃት ሊመልሱት የሚችሉት የጉዳዮቹ ባለቤቶች ምሁራኖቿና አናብስቷ ናቸው ። እነርሱ እራሳቸው ይህንን ጥያቄ በጥልቀት ሊያዩት ይገባቸዋል ። ሌላው ቢቀር፥ የአናብስት ሀገር፥ በሀገር ሻጭ ከሃዲዎች መገዛት አልነበረባትም !

አንዳንድ የማይታበሉ ሀቆችን ያለመታከት  ስናወሳ  መቆየታችን የሚካድ ባይሆንም፥ ዛሬም እነዚህን ሀገራዊ ጉዳዮች በግልፅ በመናገራችን የተወሰኑ ንዑሳን ክፍሎች እንደሚጎረብጣቸው ይሰማናል ። ቢሆንም፥ በትግል ሂደት፥ ሕዝብ ማወቅ ያለበትን ብሔራዊ ጉዳይ  ማሳወቅ ፥ የትግሉ አካል በመሆኑ፥ ያንን ከማድረግ የምንቆጠብ አንሆንም። ይህንን መገንዘብ ካለብን ፥ በትግሉ ሂደት  የታዘብነውን ስንታዘብ ፥ ትዝብቱን ደግሞ በአርምሞ  ለማለፍ እንቸገራለን ። በተቃዋሚው በኩል በአመዛኙ የትግሉ ጊዜ የባከነው፥ በወያኔ ድርጊትና ፖሊሲ ላይ ምላሽ በመስጥት ያተኮረ ነበር እንጅ፥በራሱ አነሳሽነት ወያኔን የሚያርበተብት ተግባር ያስመዘገበው ውጤት ይህን ያህል ነበር  ብሎ ለመናገር የሚቻል አልሆነም ። ይህም ሀቅ ፥ ወያኔዎቹ የረባ ተቃዋሚ አጣን ብለው ለመመፃደቅ የሚያስችላቸውን ሀኬት እንዲናገሩ አድርጓቸዋል። ወያኔን ያህል ዘረኛ ሥርዓት የሚያራምድ የሀገር  ጠላት ፥  በነባቢት  ብቻ  ሳይሆን በሚያደማ ድርጊት ጭምር መታገል፥ ወቅቱ የሚጠይቀው አንገብጋቢ ሀገራዊ ጉዳይ ነው ። ይኸንንም ደጋግሞ ማስረዳት የሚያሻ አይሆንም ። ደርግ  ወደ ሥልጣን በወጣበት የመጀመሪያው ዓመት "ደርግ አንድ ሐሙስ ቀርቶታል " ሲባል እንደነበረ የሚያስታወስ  ያስታውሰዋል። ዛሬም እንደ ትላንቱ "ዘረኞቹ ሊሄዱ ጥቂት ቀርቷቸዋል" የሚለው የማቋመጥ ጉጉት በተግባር ካልተደገፈ፥ ውጤት ሊያስመዘግብ እንደማይችል መገንዘብ ብለኅነት ነው ። በሌላ  በኩል ደግሞ ፥ ተጨባጩ ሁኔታ በትክክል የሚያመለክተው ፥ ወያኔዎች ወደ ከርሰ

መቃብራቸው የሚገቡበት  ወቅት  ሩቅ  እንዳልሆነ ነው::  የሀገሪቱ  ነባራዊ ሁኔታዎች የሚጠቁሟቸው አቅጣጫዎች ሁሉ ወደ ጥፋቱ  ጎዳና ያመለክታሉ::

- በዓለም ላይ በደረሰው ከባድ የኢኮኖሚ ችግር ምክንያት  የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ  በአስጊ ሁኔታ ነጥፏል:: ከውጭ የሚገቡት እቃዎች እንደ መድኀኒት ፥  የመለዋወጫ  ዕቃዎች ፥ ነዳጅ፥ ሌሎች እጅግ አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች እና   በውጭ ምንዛሬ ሊገዙ የሚችሉት ከባድና ቀላል  ሸቀጦችን ለማስገባት አልተቻለም:: የዓዜውን ሥርዓት ከገረሰሱት  ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ፥ የነዳጅ ዋጋ መጨመርና የውጭ ምንዛሬ መጥፋት እንደነበር የቅርብ ትዝታ ነው ::ወያኔ ከዚህ የታሪክ ምፅዓት - ክስተት ሊያመልጥ ከቶ  አይችልም ::  እባካችሁ ቦንድ ግዙኝ  የሚለው  ልመናም   ትዕዛዝም   ከማይቀረው  እሳተ-ገሞራ አያድነውም::

- የሥራ አጡ  ቁጥር ሰማይ ጠቀስ ሆኗል:: እንደ ኢኮኖሚ ጠበብቶች ጥናት ከሆነ ፥ በአዲስ አበባ ብቻ አራት መቶ ሽህ የሚሆኑ ወጣቶች ሥራ ፈት ሆነው በችግር እንደሚማቅቁ ተረጋግጧል ::    የዋጋው ውድነት፥ የገንዘቡ ግሽበት፥ የዕለት ጉርስ እጦት፥ የማህበራዊው ኑሮ ቀውስ ፥ የከተማዎች  በሕዝብ   ብዛት    መጨናነቅ   ከየሥራው የሚፈናቀለው ሰራተኛ ብዛት ፥ የወያኔ የፖለቲካ ፥ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ  ኑሮ መዋቅር  ከሚያስተናግደው  በላይ  ሆኗል  :: ከዚህ ጋር  ተያይዞ መታየት ያለበት በአገዛዙ ቁንጮዎች የታቀፈው ወንጀለኛ ብዛትና የወንጀሉ ዓይነት ነው::  ይህ  ደግሞ  ለአንድ  ሀገር የጤንነት ምልክት ሊሆን አይችልም::

- የወያኔ የበላይ ጠባቂዎችና  ምዕራባውያን  ደጋፊዎቹም ፥ እንኳንስ ሊረዱት ቀርቶ እራሳቸው ከገቡበት ማጥ ሊወጡ አልተሳካላቸውም :: የሁሉም ሀገር መሪ ቅድሚያ የሚሰጠው ለራሱ ሀገር መሆኑን ማንም

የሚያውቀው ሀቅ ስለሆነ ያንን መዘርዘር አይኖርብንም ። ወያኔዎች ግን የእኛ የሚሏት ሀገር ስለሌላቸው ፥ ይህንን ሀቅ ሊገነዘቡት አይችሉም።

- የወያኔ ሠራዊት ያምፅ ይሆናል ተብሎ በመፈራቱ መለስና ግብ አበሮቹ ወታደራዊ መዋቅራቸውን በየጊዜው በመበወዝ ላይ ይገኛሉ ። ከከፍተኛ መኮንኖች በታች ያለውን ነባር ወታደር እያሰናበቱ በአዳዲስ ምልምል እየተኩት ይገኛሉ ። ይኸም ዘዴ ለጊዜውም ቢሆን በበታች መኮንኖችና በባለ ሌላ ማዕረጎች አማካኝነት ሊቀሰቀስ የሚችለውን አመፅም ሆነ መፈንቅለ መንግሥት ለመካለከል ታስቦ ነው ።

- አሁን በሀገሪቱ የሚታየው የፀጥታ ሁኔታ በደርግ የመጨረሻው ሰዓት ከነበረው ሁኔታ ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይነት ይነበብበታል። የወያኔ ባለሥልጣናትም " ምናችን ሞኝ ነው " ስለሚሉ አስቀድመው መውደቂያቸውንና የሽሽታቸውን ሁለንተናዊ ሂደትና ዝግጅት አጠናቀው ጨርሰዋል ። የወያኔው ጳጳስ አባ ፓውሎስ ተብዬው ሳይቀር " ልጆቼ እባካችሁ ለእኔም ፓስፖርቴን አዘጋጁል ኝ" አሉ የተባለው ፥ ለቧልት የተነገረ ነው ተብሎ የሚታለፍ አይደለም ። ለአለፉት 18 ዓመታት ሁሉም በየፊናው የሰራውን ስለሚያወቅ መገልበጫውን አዘጋጅቶ እንደሚጠብቅ ሳይታለም የተፈታ ሆኗል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለነገዋ ኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ሁኔታዎች አበክሮ እንዲያስብበት ማሳሰብ ፥ ከዜግነት ግዴታችን አንዱ ክፍል ስለሆነ ለወሳኙና ለቁርጠኛው ትግላችን እየተዘጋጀን እያለን ፥ ሀገሪቱን አጥፍተው ለመጥፋት በዝግጅት ላይ ያሉትን ዘረኞች የዕለት ተዕለት ሂደታቸውን በቅርብ እንዲከታተል ጥሪያችንን ለሁሉም ዜጋ

እናስተላልፋለን። ትላንት እነርሱ፥ “ ውሾቹም ይጮኻሉ፥ ግመሎቹም ይጓዛሉ ” የሚል ምፀት መናገራቸውን እያስታወስን፥ እኛም ዛሬ ፥ “ ግመሎቹ ሲከስሙ፥ ኢትዮጵያ ትፋፋለች” እንላለን። ለነገሩ ዓይኑ ከተሸበበ ግመል እዚያው በዚያው ዘይት መጭመቂያ እየጎተተ ሲዞር ፀሐይ ትጠልቃለች። ይህ ደግሞ ለመፈክራቸው ምላሽ ለመስጠት ሳይሆን፥ የማይቀረውን የነፃነት ጮራ ለመፈንጠቅ ነው።

**ልብ ያለው ልብ ይበል!!!**